# ግንቦት 7 ሲዘከር

ዛሬ ግንቦት 7 2003 ዓ.ም. ነው። ይህ ቀን ለኢትዮጵያዊያን ያለው ትርጉም ከፍተኛ ነው።

ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ የነበረው ተስፋና የልበ-ሙሉነት ስሜት የምናስታውሰው ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በላዩ ላይ የተጫነበትን አገዛዝ በምርጫ ካርዱ አባሮ ይበጀኛል ያላቸውን ለመምረጥ ያለውን ጉጉት እና ችሎታ ለመላው ዓለም ያረጋገጠበት ቀን ነው - ግንቦት 7 ቀን 1997። በዚያ ቀን በተደረገው ምርጫ እና ድምጽ በአግባቡ በተቆጠረበት ጣቢያ ሁሉ የመለስ ዜናዊ ድርጅት ድርሻ ከአስር በመቶ ያነሰ ነበር።

በእለቱ በህዝቡ ልብ ውስጥ ውስጥ የነበረው የአንድነት፣ የመቻቻል፣ የወንድማማችነትና የእህትማማችነት ስሜቶችም ፈጽሞ የሚዘነጉ አይደሉም። ሆኖም የአዲስ አበባው ውጤት እንደታወቀ ከአዲስ አበባ ውጭ የነበረው ድምጽ ተዘረፈ። ገለልተኛ ነፃ የሆነ የምርጫ ቦርድ፣ የጦር ሠራዊት፣ የሚዲያ እና የፍትህ ተቋማት በሌሉበት በህዝብ ድምጽ የተባረረው መለስ ዜናዊ በአግዓዚ ሠራዊት ድጋፍ ሥልጣን እንደያዘ ቆየ። ያ ሁሉ ተስፋ በጉልበት ተደፈጠጠ። ምርጫ 97ን ተከትለው የመጡ የአፈና እርምጃዎች የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫዎች ለማድረግ አንዳችም ፍላጎት እንደሌለው፤ በየጊዜው የሚደረጉ ምርጫዎችን የሚፈልጋቸው ለአገዛዙ ህጋዊ እውቅና ለመስጠት ብቻ መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ አሳዩ።

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ በጉልበት የተነጠቀውን መብት ማስመለስን ዓላማው ያደረገ፤ በኢትዮጵያ የፓለቲካ ታሪክ ውስጥ በዚህ የፓለቲካ ዓላማው ልዩ የሆነ ንቅናቄ ተወለደ። ንቅናቄው ግንቦት 7 1997ን ለመዘከር ሲልም ራሱን "ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ" ሲል ሰየመ።

ግንቦት 7 ቀን 1997 በኢትዮጵያ የነበረው ተስፋ የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እስትንፋስ ነው። ዓላማውም ያንን ተስፋ ህያው ማድረግ ነው። ኢትዮጵያዊያን ተዓማኒነት ባለው ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ መንግሥታቸውን መሾም እስከሚችሉ ድረስ የግንቦት 7 ትግል ይቀጥላል።

በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሥር ኢትዮጵያዊያን የሚደርስብን የመብት ረገጣ በእለት ወደእለት እየከፋ መጥቶ ዛሬ የከፋቱ መጠን ልክ አጥቷል። የህዝባችን የኑሮ ሁኔታም በከፍተኛ ፍጥነት እያሽቆለቆለ ነው። ሁኔታዎች በአንክሮ

ያስተዋለ ሁኔታ አገራችን ከግንቦት 7 ሁለ-ገብ የትግል ስልት አንዱ ለሆነው ለህዝባዊ እምቢተኝተኝነት እየተዘጋጀት እንደሆነ ይገነዘባል። እየመጣ ያለውን ህዝባዊ እምቢተኝነትን በድል ለማጠናቀቅ ደግሞ ሁለ-ገብ ዝግጅት ያስፈልጋል፤ ለዚህም ድርጅታችን የሚያስፈልገው እያደረገ ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!!